የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

በኢንፎሜሽንና ኮ/ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ከመጋቢት 1- 8፣ 2018 ዓ.ም
MARCH 10 -17/2026

1. የቡና ምርት ዋጋ ይጨምራል በሚል ኢ-ሳይንሳዊ የገበያ ትንበያ ምርት ያከማቹ አካላት ምርታቸውን ለማዕከላዊ ገበያ ማቅረብ አለባቸው - ግብርና ሚኒስቴር

ኢዜአ፡ መጋቢት 2/2018

የቡና ምርት ዋጋ ይጨምራል በሚል ኢ-ሳይንሳዊ የገበያ ትንበያ ምርት ያከማቹ አካላት ምርታቸውን ለማዕከላዊ ገበያ ማቅረብ እንዳለባቸው የግብርና ሚኒስቴር አሳሰበ።

የግብርና ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈፃሚ ይመር ዳውድ፤ ኢትዮጵያ ቡናን በጥራትና በመጠን በማምረትና ለዓለም ገበያ በማቅረብ የተሻለ ገቢ ማግኘቷን አስታውሰዋል።

የቡናን ዕሴት ሰንሰለት በማሳለጥና ምርታማነትን በማሳደግ የተመዘገቡ ስኬቶች ለዘርፉ እመርታዊ ገቢ ከፍተኛውን ድርሻ መውሰድ እንዳስቻለ አስረድተዋል።

የዓለም የቡና ገበያ በከፍተኛ ሁኔታ ዝቅ ብሏል ያሉት ሥራ አስፈፃሚው፤ በዚህም አምራቾች ሊደርስ የሚችልን ኪሳራ ታሳቢ በማድረግ ምርታቸውን ለማዕከላዊ ገበያ እንዲያቀርቡ አሳስበዋል።

ቡና አምራቾችና ላኪዎችም በተሳሳተ ስሌት ምርትን ከማከማቸት ይልቅ ወቅታዊ የገበያ ሁኔታን ታሳቢ በማድረግ የእራሳቸውንና የሀገርን ገቢ ከሚጎዳ ተግባር መቆጠብ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

ይህንን ለመከላከል የተቋቋመው ግብረ ኃይል ከክልል ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ዋጋ ይጨምራል በሚል የቡና ምርት ይዘው ባከማቹ አካላት ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንደሚወስድ አስታውቀዋል።

ኢ-ሳይንሳዊ በሆነ የገበያ ትንበያ ላይ ተመስርተው ከዘርፉ ገቢ እንዳይገኝ የሚያደርጉ አካላትም በሕግ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ተናግረዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_8463980

2. ሚኒስቴሩ ለሦስት ኩባንያዎች የማዕድን ምርት ፍቃድ ሰጠ

ኤፍ.ኤም.ሲ ፡ መጋቢት 4፣ 2018

ማዕድን ሚኒስቴር በተለያዩ የማዕድን ምርት ለሚሰማሩ ሦስት ኩባንያዎች የምርት ፍቃድ ሰጥቷል።

የማዕድን ሚኒስትር ሀብታሙ ተገኝ (ዶ/ር) በዚህ ወቅት እንዳሉት፥ ኢትዮጵያ በማዕድን ዘርፍ ያላትን ሀብት በተገቢው መንገድ ለማልማት ወሳኝ ርምጃዎችን እየወሰደች ትገኛለች።

ለኩባንያዎቹ ፍቃድ መሰጠቱ ማዕድናቱን ወጥነት ባለው መልኩ ለማምረትና ወደ ውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪን ለማስቀረት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው አብራርተዋል።

በተጨማሪም ስትራቴጂያዊ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት የምርት ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ አቅም የሚፈጥር ነው ብለዋል።

ፍቃድ የተሰጣቸው ኩባንያዎች በፖታሽ፣ በብረትና በወርቅ ማዕድን ምርቶች የሚሰማሩ ሲሆን፥ ሦስቱም የማዕድን ምርቶች 4 ነጥብ 2 ቢሊየን ዶላር ኢንቨስትመንት ወጪ የሚደረግባቸው መሆናቸው ተገልጿል።

በዚህም መሰረት በፖታሽ ምርት ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ፣ በብረት ምርት ለዜድዋይቲ ቢዲአይኤም (ZYTBDIM) እንዲሁም በወርቅ ምርት ለቤሮ ማይኒንግ የማዕድን ምርት ፍቃድ ተሰጥቷል።

https://www.fanamc.com/archives/311123

3. የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ የገቢና ወጪ የንግድ እንቅስቃሴዎችን በላቀ ብቃት የማሳለጥ ተልዕኮውን አጠናክሮ ቀጥሏል

ኢዜአ፡ መጋቢት 2/2018

የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ የገቢና ወጪ የንግድ እንቅስቃሴዎችን በላቀ ብቃት የማሳለጥ ተልዕኮውን አጠናክሮ መቀጠሉን የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ብሩክ ታዬ (ዶ/ር) ተናገሩ።የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ 100 ዘመናዊ የከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎችን ሥራ አስጀምሯል።

የከባድ መኪናዎችን ቁልፍ ከሲኖ ትራክ ኩባንያ የኢትዮጵያ ተወካይ ተረክበው ስራ ያስጀመሩት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ብሩክ ታዬ (ዶ/ር) እና የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ኢንጂነር አብዱልበር ሸምሱ ናቸው። ብሩክ ታዬ (ዶ/ር) በወቅቱ እንዳሉት፤ በሆልዲንጉ ስር ከሚገኙ ተቋማት አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ የባህርና ትራንስፖርት ሎጂስቲክስ የኢትዮጵያን ብልፅግናና ዕድገት በሚመጥን ከፍታ ኃላፊነቱን እንዲወጣ በቅንጅት እየተሰራ ነው። የኢትዮጵያን የወጪና ገቢ እንቅስቃሴዎች ለማሳለጥ ወሳኝ አበርክቶ ያለውን ድርጅት በዘመናዊ አደረጃጀትና አሰራር በማገዝ የላቀ እና የተሳለጠ አገልግሎት እንዲሰጥ እየተሰሩ የሚገኙ ተግባራት ውጤታማ መሆናቸውን ገልፀዋል።

ወደ ስራ የገቡት 100 ዘመናዊ ከባድ መኪኖች የዚሁ ማሳያ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በቀጣይም ኢትዮጵያ ያላትን የተፈጥሮ ጋዝ የሚጠቀሙ 100 ዘመናዊ ከባድ ተሽከርካሪዎች ወደ ስራ ለማስገባት ዝግጅት መደረጉን ተናግረዋል። እየተሰሩ ያሉ ተግባራት የጭነት ተሽከርካሪ ዕጥረትን በመፍታት በዘርፉ ተመራጭ የአፍሪካ ድርጅት የመሆንን ጉዞ የሚያሳኩ መሆኑን በመግለፅ።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_8465134

4. ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ነዳጅን በኃላፊነትና በቁጠባ እንድንጠቀም አሳሰቡ

ኢቢሲ፡ ሰኞ መጋቢት 07, 2018

በመካከላኛው ምሥራቅ በተፈጠረው ቀውስ የተነሣ ነዳጅ ገዝተው የሚጠቀሙ ሀገሮች እንደልብ ለማግኘት ተቸግረዋል።

በመሆኑም ችግሩ ተፈትቶ ወደ መደበኛው የነዳጅ አቅርቦት ሥርዓት እስከንመለስ ድረስ ነዳጅን በቁጠባና ለመሠረታዊ ነገሮች ቅድሚያ በመስጠት መጠቀም ይኖርብናል።

በመሆኑም የነዳጅ አከፋፋዮች፣ማደያዎች እና ተጠቃሚዎች ነዳጅን በቁጠባ፣ ለመሠረታዊ ነገሮች ቅድሚያ በመስጠት ሁላችንም በሃላፊነት ስሜት እንድንጠቀም ለማሳሰብ እወዳለው ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)።

https://www.ebc.et/Home/NewsDetails?NewsId=4477

5. Businesses Raise Concerns over Minimum Alternative Tax, Quarterly Tax Payments

The Reporter: March 14, 2026

Business taxpayers raised concerns over the minimum alternative tax (MAT), quarterly tax payment requirements, and stricter bookkeeping rules during a public consultation held this week by the Ministry of Finance on a draft income tax regulation.

The consultation, convened on March 10, sought feedback from private sector representatives and professionals on a draft regulation intended to implement the recently amended Federal Income Tax Proclamation. The meeting was chaired by Tewodaj Mohammed, director of Legal Affairs at the Ministry.

Following a presentation outlining the regulation's provisions, participants from multiple business sectors raised questions about its implementation, with several warning that the proposed measures could discourage business activity and place additional strain on industries already facing economic pressure.

One of the most debated provisions was the minimum alternative tax, which is designed to apply to taxpayers who report losses. The draft regulation proposes that businesses declaring losses still pay a tax equivalent to 2.5 percent of their total turnover.

https://www.thereporterethiopia.com/49698/

6. Economic Reforms Position Ethiopia as Emerging Investment Hub, Says Minister Kassahun

ENA : March 16, 2026

Ethiopia's Minister of Trade and Regional Integration, Kassahun Gofe underscored that the country is rapidly emerging as an attractive destination for investors as sweeping economic reforms continue to reshape the business environment.

Speaking at a panel discussion titled "Ethiopia: The New Investment Destination," organized by the Ethiopian News Agency in collaboration with the Ethiopian Investment Commission, the minister highlighted the government's efforts to expand investment opportunities and strengthen private sector participation.

Kassahun emphasized that investment plays a critical role in accelerating Ethiopia's economic transformation.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_8495223

7. Tax Pressures, Logistics Hurdles Weigh on Pulses and Oilseeds Exports

Capital: March 15, 2026

Contrary to expectations that the recent macroeconomic reforms would stimulate growth, Ethiopia's export sector—excluding a few specific goods—is currently underperforming. This shortfall was a central topic in a high-level, closed-door meeting convened on Saturday, March 7, by the Ministry of Trade and Regional Integration (MoTRI).

The meeting was called to address concerns raised by the Ministry of Revenue (MoR) regarding the impact of newly implemented tax regulations on exporters, who report that the measures are straining their financial operations.

The gathering brought together MoTRI leadership and exporters, primarily those operating within the ministry's direct oversight. While commodities such as coffee and gold fall under the purview of other regulatory bodies, MoTRI is responsible for shepherding the export of pulses and oilseeds, a sector that has historically been a significant contributor to Ethiopia's commodity export revenues.

A primary point of contention raised by exporters was the implementation of the Minimum Alternative Tax (MAT), introduced in the previous budget year. As stipulated in Article 23 of Proclamation No. 1395/2024, taxpayers are required to pay a minimum tax if their total assessable business income for a year results in a tax liability below 2.5 percent of their annual turnover

Exporters argue that while their business involves high transaction volumes, their net profit margins remain low. Consequently, they perceive the MAT as a disproportionate burden. "The turnover is significant, but our earnings are not," one exporter explained. "The MAT poses a substantial risk to our business because it is based on revenue rather than actual profit."

https://capitalethiopia.com/2026/03/15/tax-pressures-logistics-hurdles-weigh-on-pulses-and-oilseeds-exports/

8. Businesses Face 2.6 Trillion Birr Financing Gap, Study Finds

The Reporter: March 14, 2026

Ethiopian micro, small and medium enterprises (MSMEs) are facing a severe shortage of finance and business premises, with a new study estimating the country's credit gap at 2.6 trillion Birr, experts said during a forum held yesterday in the capital.

The research was presented at a public-private dialogue organized by the Addis Ababa Chamber of Commerce and Sectoral Associations at Capital Hotel and Spa, where policymakers, financial institutions and business leaders gathered to discuss challenges hindering private sector growth in Addis Ababa.

https://www.thereporterethiopia.com/49689/